እሥረኛው ባለ ታሪክ

አንዳንዶች በድሎትና በምቾት ላይ ያገኙትን የሰላም ዘመን ምንም ሳይጠቀሙበት ‹ተወለዱ- ሞቱ› ተብለው ያልፋሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ስደታቸውን፣ እሥራቸውንና ግዘታቸውን፣ መከራቸውንና ሕመማቸውን የሀገርንና የወገንን ታሪክ ለመለወጥ፣ በሰው ልጅ ታሪክም ውስጥ ጉልሕ ቦታ ለመያዝ ሲጠቀሙበት ይታያሉ፡፡ እኛ ‹የመከራ በረከት› ፈረንጆች ‹blessing in disguise› የሚሉት ማለት ነው፡፡ ሰውን የሚጎዳው የደረሰበት ችግርና መከራ አይደለም፡፡ በዚያ ችግና መከራ ውስጥ ሆኖ የሚያየው ነገር ነው፡፡ ገነት ውስጥ ሆነው ሲያልን ከሚያዩ ሰዎች ይልቅ ሲያል ውስጥ ሆነው ገነትን የሚያዩ ሰዎች ይበልጣሉ፡፡ አንዳንዶች በመታመማቸው ምክንያት ታሪክ ሠርተዋል፡፡ አንዳንዶች በመታሠራቸው ምክንያት ታሪክ ሠርተዋል፤ አንዳንዶች በመሰደዳቸው ምክንያት ታሪክ ሠርተዋል፤ አንዳንዶችም በመቸገራቸው ምክንያት ታሪክ ሠርተዋል፡፡

ችግር ሁለት ነገሮችን ትወልዳለች፡፡ ጠቢባን ሲያዋልዷት ብልሃትን፣ ሞኞች ሲያዋልዷት ድህነትን፡፡

ችግርን ቀምሰዋት፣ በጥበብም አዋልደዋት ብልሃትን እንድትወልድ ካደረጓት የሀገራችን ሰዎች አንዱ ደጃዝማች ኃይሉ እሸቴ ናቸው፡፡ ዘመነ መሳፍንት ተብሎ በሚጠራው የሀገራችን ዘመን አብዛኛውን ዘመናቸውን የሳለፉት የአስተዳደር፣ የጦርና የቀለም ሰው ደጃዝማች ኃይሉ እሸቴ የተወለዱት በ1746 ዓም አካባቢ ጥር 12 ቀን ነው፡፡ አባታቸው ደጃዝማች እሸቴ እናታቸውም ወ/ሮ ወለተ ራጉኤል ይባላሉ፡፡

ደጃዝማች ኃይሉ በዘመኑ እንደነበሩት የኢትዮጵያ የመኳንንት ልጆች ፈረስ ግልቢያውንና አደኑን እየተማሩ፣ የቀለም ትምህርቱንም ጎን ለጎን እያስኬዱ አደጉ፡፡ በዚህ መካከል ግን መጋቢት ፲፱ ቀን 1760 ዓም አባታቸው ደጃዝማች እሸቴ በጦርነት ላይ ሞቱባቸው፡፡ ያኔም እድሜያቸው ወደ አሥራ አራት ዓመት ያህል ሆኗቸው ነበር፡፡ ወላጅ እናታቸው በ1755 ዓም የሞቱባቸው ኃይሉ እንደገና የአባታቸው በልጅነታቸው መሞት ኀዘኑን አጸናባቸው፡፡

ዘመነ መሳፍንት ግም ግም ሲልና ከትግራይ የመጡት ራስ ሚካኤል ስሑል መንግሥቱን እየጠቀለሉት ሲመጡ፤ በጎንደር ከተማም በቋረኞቹና በኦሮሞዎቹ መካከል ንጉሡን ኢዮአስን ይዘው መንግሥቱን ለመቆናጠጥ የፖለቲካው ትግል ሲያይል፣ ኃይሉ እሸቴ የራስ ሚካኤል ስሑልን ልጅ ወለተ ጥሪለ ሃይማኖትን አግብተው የራስ ሚካኤልና የቋረኞቹ ደጋፊ መሆናቸውን አሳዩ፡፡ ራስ ሚካኤል ስሑል በጎንደር ቋረኞችን ይዘው ሥልጣን ሲያደላድሉ፣ ደጃች ልቦ እና ደጃች ፋሲል ከተባበሯቸው ከይልማና ዴንሳ፣ ከሜጫ፣ ከዳሞትና ከወሎ ተወላጆች ጋር ሆነው ሸፈቱ፡፡ የተወሰኑት ቋረኞችም ተከተሏቸው፡፡ ራስ ሚካኤልም አስገብራለሁ ብለው፣ ደጃዝማች ኃይሉም የአባታቸውን ሞት ለመበቀል አብረዋቸው ዘመቱ፡፡ የመጀመሪያውን የታወቀ ጀብዷቸውንም በዚህ ጦርነት ላይ አሳዩ፡፡ የዘመኑ ገጣሚም

ጎራዴማ ወትሮ እንዲመታ ዐውቃለሁ፣

እኔ ኃይሉን እንጂ አመሰግናለሁ፤

ብሎ ገጠመላቸው፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ደጃዝማች ኃይሉ ተፈሪነታቸውና ተሰሚነታቸው እየጨመረ፤ በግዛትም ላይ ግዛት እየተሸሙ ኖሩ፡፡ በተደጋጋሚ በየጦርነቱ ባሳዩት ጀብዱ እየተገጠመላቸው፣ ግዛትም እየተጨመረላቸው፤ የራስ ሚካኤል ስሑል ዘመን ሲያልፍም ከመጭውቹ ኃያላን ጋር እየተስማሙ እስከ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ዘመን እየተወደዱና እየተሞገሱ ቀጥለው ነበር - ደጃዝማች ኃይሉ፡፡

በአንድ በኩል የዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ዘመን በ1771 ዓም ሲጀምር የደጃዝማች ኃይሉ የተወዳጅነትና የተከባሪነት ዘመን በሌላ በኩል ማዘቅዘቅ ጀመረ፡፡ በተክለ ጊዮርጊስና በሰሎሞን መካከል በቤተ መንግሥት የሥልጣን ሽኩቻ ተፈጠረ፡፡ በመጨረሻም ደጃች ከንፉ የሰሎሞንን ዋና ደጋፊ ራስ ኃይሉን ወግተው ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስን አነገሡ፡፡ በዚህ ጊዜ ደጃዝማች ኃይሉ

www.danielkibret.com

የዘመነ መሳፍንት ሁከትና ውጊያ ሲሰለቻቸው ካልመጡብኝ አልሄድም ብለው ዐርፈው ተቀምጠው ነበር። ደጃች ከንፉ ራስ ኃይሉን ለመውጋት ሲዘምቱ ደጃዝማች ኃይሉ አብረዋቸው እንዲዘምቱ ልከውባቸው ነበር። ደጃዝማች ኃይሉ ግን ፈቃደኛ አልሆኑም። ይህም በአሸናፊዎቹ በእነ ደጃች ከንፉ ዘንድ ጥርስ አስነከሰባቸው።

ከጦርነቱ በኋላ በንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስና በደጃች ከንፉ ታዝዘው ደጃዝማች ኃይሉ ወደ ጎንደር መጡ። የጠበቃቸው ግን ጎጃም ቡሬ ላይ በቁም እሥር መቀመጥ ሆነ። እርሳቸውም ቡሬ ላይ ጥቂት ከቆዩ በኋላ ጠፍተው ሲሄዱ ደጃች ከንፉ ፈረሰኛ ልከው አቸፈር ላይ አስያዟቸውና በሠንሠለት ታሥረው ጎንደር ገቡ። እርሳቸው ታሥረው ጎንደር ሲገቡ የጎንደር ሕዝብ በእጅጉ ማዘኑን ታሪክ ነገሥቱ ይነግረናል። የዋልድባ መነኮሳትም ኃይሉን ለማስፈታት ምልጃ ገብተው ነበር። ንጉሡም ከዛሬ ነገ እፈታለሁ እያሉ ዝም ብለው አስቀመጧቸው።

የጎንደሩ የቁም እሥር ያልተመቻቸው ደጃዝማች ኃይሉ በሌሊት ጠፍተው ማጎደረ ማርያም ገቡና የተማጽኖ ደወል መቱ። ኃይሉ በደኅናው ዘመን ከታላላቅ ገዳማትና አድባራት አባቶች ጋር በጎ ግንኙነት ነበራቸው። እርሳቸውም የዘመኑን ትምህርት የተማሩ ነበሩና በእነዚህ ታላላቅ አባቶች ዘንድ ተሰሚነት ነበራቸው። ደጃዝማች ኃይሉ በእቴጌ ማርያም ሥና በተደበረችው ማጎደረ ማርያም ለአራት ዓመት ከሦስት ወር ነበር በግዞት የተቀመጡት። በኢትዮጵያ ታሪክ በሰላሙ ዘመናቸው በጦርነትና በአስተዳደር ካበረከቱት አስተዋጽዖ ይልቅ ኃይሉን ሲያስጠራቸው የሚኖረው በዚህ በግዞትና በመከራ ዘመናቸው ለሀገራቸው የሠሩት ተመን የማይገኝለት ሥራቸው ነበር።

ራስ ኃይሉ በማጎደረ ማርያም ሲቀመጡ ከሁካታውም ከጦርነቱም ጋብ አሉ። ሀገር ለሀገር ከመዞር ዐርፈው ወደ ልባቸው ተመለሱ። በደብሩ የሚከናወነው ጸሎትና ትምህርትም ጽሞናን ሰጣቸው። በዚያ ዘመን ማንም ሊታየው ያልቻለውን ዘመን ተሻጋሪ ራእይም አዩ። ሀገሪቱ በግራኝ አሕመድ ጊዜ ከገጠማት የርስ በርስ ጦርነት ወጥታ ወደ ሌላ የርስ በርስ ጦርነት ገብታለች። በጎንደር ከተማ የሚደረገው የሥልጣን ትግል ከምንም በላይ የጎዳው ሕዝቡንና የሕዝቡን ታሪክ ነው። በተለይም ደግሞ ለብዙ ዘመናት በየቤተ መንግሥቱ፣ በየገዳማቱና አድባራቱ የተከማቹ መዛግብት በጦርነቱ ምክንያት ይቃጠላሉ፤ ይቆነጻጸላሉ። ኃይሉ በንሥር ዓይናቸው ይህንን ነበር ያዩት።

‹በሰንበት ላይ ደብረ ዘይት፣ በእራት ላይ ዳረጎት› እንዲሉ ኃይሉ ይህንን ሲያስቡ የሸዋው ተወላጅ ጽሕፈት ዐዋቂው አቤቶ አበጋዝ ወደ ማጎደረ ማርያም መጣ። ደጃዝማች ኃይሉ እሥርና ግዞቱን ወደ ታላቅ የጥናትና ምርምር ተቋምነት ቀየሩት። ከየገዳማቱና ከየሊቃውንቱ እየተላላኩ የታሪክ መዛግብትን እያስመጡ፣ እያመሳከሩና እየጠየቁ ስማቸውን እስከ ዓለም ፍጻሜ የሚያስጠራውን፣ ዛሬ በፓሪስ ቤተ መጻሕፍት በቁጥር 143 ተመዝግቦ የሚገኘውን፣ በአራት አዕማድ ተጽፎ፣ በ370 ገጽ በብራና የተዘጋጀውን ‹ታሪክ ነገሥት ዘደጃዝማች ኃይሉ እሸቴ› የተባለውን የኢትዮጵያ የታሪክ መጽሐፍ አዘጋጁ። ለሦስት ዓመታት ያህል መረጃዎችን ሲያሰባስቡ፣ መጻሕፍቱን ሲያመሳክሩ ቆይተው፣ ለአንድ ዓመት ያህል ተጽፎ በ1778 ዓም መስከረም ሰባት ቀኝ ቸጠናቀቀ።

ደጃዝማች ኃይሉ ከማጎደረ ማርያም ግዞት በኋላ እንደ ጥንቱ ባይሆንም እየተሾሙ ለጥቂት ጊዜ ቆይተዋል። በተለይ በራስ ዓሊ ጊቤ ብሜንንና በጌምድን እየተሾሙ በደስታ ኖረዋል። ራስ ዓሊ ሲሞቱ ግን ከቀጣዩ ባለ ሥልጣን ከራስ ወልደ ጉብርኤል ጋር መስማማት ባለመቻላቸው በስደት ወደ ጎጃም ወደ ራስ መርእድ ዘንድ ሄዱ። በዚያ ሆነው ወደ ሀገራቸው የሚመለሱበትን ዘመን ሲናፍቁ መርዕድና ወልደ ጉብርኤል ሐምሌ 15 ቀን 1791 ዓም ባደረጉት ውጊያ ሁለቱም ራሶች ሲወድቁ የድሉ ሚዛን ወደ ራስ ወልደ ጉብርኤል ሰዎች ዞረ።ደጃዝማች ኃይሉም ወደ ርስቴ እመለሳለሁ የሚለው ተስፋቸው ተቆረጠ።

ደጃዝማች ኃይሉ የሕይወታቸውን ፍጻሜ ያሳለፉት ጎጃም ሞጣ ነው። እዚያ ምናልባት እስከ 1810 ዓም አካባቢ የቆዩ ይመስላል። ሞጣ እያሉ ታላቁ የውጊያና የታሪክ ሰው ታምመው ሞቱ። ወገኖቻቸውም ሬሳቸውን ይዘው ራሳቸው ወዳሠሩት

www.danielkibret.com

ወደ እስቴ መካነ ኢየሱስ ለመቅበር መጡ፡፡ ዘመነኞቹ የራስ ጉግሣ ሰዎች ግን ሬሳውን አናሳልፍም ብለው እምቢ አሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ልጃቸው ወ/ሮ ምርጪት ፡-

እግዚኦ አቤት አቤት

እግዚኦ አቤት አቤት

አፈር ይለምናል የሀገሩ ባለቤት፤

ብለው ወደ ራስ ጉግሣ ደብዳቤ ጻፉ፡፡ ራስ ጉግሣም ነግ በእኔ ብለው ፈቅደው የታላቁ የውጊያና የታሪክ ሰው የደጃዝማች ኃይሉ መጨረሻ በእስቴ መካነ ኢየሱስ ተፈጸመ፡፡ በክፉ ዘመን ሰብስበው በማጻፍ ለዘመናችን ያበረከቱልን ታሪክ ነገሥት ግን ዘመንን እየተሻገረ እስከ ዘመናችን ዘልቋል፡፡ ለነገም ይኖራል፡፡ በችግራቸው የሚቆዝሙ፣ በመከራቸው የሚተክዙ፣ ክግንብ ባሻገር ብርሃንን ለማየት ያልታደሉ ሰዎችንም ይወቅሳል፡፡ እኛም ዜናውን ከታሪክ ነገሥታቸውና ተክለ ጸድቅ መኩሪያ ከጻፉላቸው አጭር ታሪክ አግኝተነዋል፡፡

www.danielkibret.com